

# መብትዎን ይወቁ

## ከሕግ አስከባሪዎች ጋር በሚገናኙት ወቅት መብትዎን ለመጠቀም መከተል ያለብዎት መመሪያ

# መብትዎን ይወቁ

## ከሕግ አስከባሪዎች ጋር በሚገናኙት ወቅት መብትዎን ለመጠቀም መከተል ያለብዎት መመሪያ

የኢሚግሬሽን ሁኔታውን/ ደረጃውን ከግምት ሳያገባ እርስዎ መብት አለዎት፡፡ እርስዎ የተመዘገቡ ሰነዶችን ከሌልዎት፣ የወንጀለኛ ታሪክ ካለዎት እና በዚያ ላይ ደግሞ ዜግነት ከሌልዎት ለመታረም ቃል ገብተው ከእስር የተለቀቁ ከሆነ፣ ወይም ከዚህ ቀደም ወደመጡበት አገር በግድ ተይዘው እንዲመለሱ ትእዛዝ የተላለፈብዎት ከሆነ አሁንም ወደ ሀገርዎ ተይዘው በግድ የመመለስ ስጋት ሊኖርብዎ ይችላል፡፡ ቤተሰብዎን፣ ራስዎን እና ህብረተሰብዎን ለመጠበቅ ስለ መብቶችዎ ማወቅ ግድ ይልዎታል፡፡

እውቀት ሃይል ነው፡፡ አሁኑኑ ይተግብሩት፡፡ ለተጨማሪ ግዜ መጠባበቅ የለብዎትም፡፡ እራስዎን ዝግጁ ያድርጉ፡፡

የዚህ መመሪያ ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው፡

- የኢሚግሬሽን ወኪሎችን፣ ፖሊስ ወይም ኤፍቢአይ (የፌደራል ምርመራ ቢሮ በተለያዩ ቦታዎች ቢገጥምዎ ምን እና ምን ማወቅ ያስፈልግዎታል፣
- የመያዣ ትእዛዝ እንዴት ማንበብ እና መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡
- በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ማወቅ የሚገባዎ አስራ ሁለት ቁም ነገሮች እና ቤተሰብዎ ማስታወስ ያለባቸው ነገሮች
- የርስዎ የድንገተኛ አስተቃቀድ መዘርዝር (ቼክሊስት)
- ስለርስዎ የድንገተኛ የመገናኛ/ ተግባቦት መፍጠሪያ መረጃ ሰነድ
- ከፖሊስ ጣቢያ ወይም ከኢሚግሬሽን ቁጥጥር ስር ማዋያ ማእከል ፍቅረኛዎ ወይም የሚወድዋቸው ግለሰቦች ስልክ ቢደውሉልዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ማቀድ
- የስራ ቦታዎ የአስተቃቀድ ቼክ ሊስት (ዝርዝር መረጃ)

*ይህ መረጃ በአጠቃላይ ለህዝቡ ግልጋሎት እንዲውል የታለመ የመመሪያ መረጃ ነው፡፡ ስለ ራስዎ የሕግ ምክር፣ ጠበቃዎን ለማማከር ወይም የተፈቀደለትን የኢሚግሬሽን ተወካይ የህግ ምክር ይጠይቁ፡፡ ተባባሪ የሆኑ ክሊኒኮችን ዝርዝር በመመልከት በ cliniclegal.org/directory በአነስተኛ ወጪ የኢሚግሬሽን ጉዳዮችን እርስዎን እንዲወክሉ መረጃ ያግኙ፡፡*



# *በየት ቦታ፡ በቤትዎ*

### ምን ማወቅ ያስፈልግዎታል:

- ወደ ቤትዎ ለመግባት፣ የኢሚግሬሽን ባለሙያዎች/ መኮንንኖች ወይም ፖሊስ የሚፈልገውን የትኛውንም 1፣ በዳኛ ወይም በአካባቢው አስተዳደር የተፈረመበት የሚያገለግል ዋስትና ወይም 2 የርስዎን ፈቃድ፡፡
- በርዎን አይክፈቱ፡፡ በር መክፈት ማለት ባለሙያዎቹ/ መኮንኖቹ ወደ ቤትዎ እንዲገቡ መፍቀድ ማለት ነው፡፡
- በቂ ምክንያት አለዎት ማለት እርስዎ ለጥያቄዎች ምላሽ መስጠት አለብዎት ማለት አይደለም፡፡
- የኢሚግሬሽን ባለሙያው ወይም የፖሊስ መኮንኑ ለእርስዎ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት እና እርስዎም መልስ መስጠት ካልፈለጉ መልስ መስጠት እንዳልፈለጉ በከፍተኛ ድምጽ ይህንኑ መንገር ወይም ለባለሙያዎቹ/ መኮንኖቹ እርስዎ ስለሙብትዎ ያወቁበትን ካርድ (ራይትስ ካርድ) እንደሚያውቁ ያሳይዋቸው፡፡

### ምን ማድረግ ይኖርቦታል:

**ደረጃ 1**

በርዎን አይክፈቱ

**ደረጃ 2**

መኮንኖቹ / ባለሙያዎቹ ወደቤትዎ ለመግባት ሙከራ ሊያደርጉ ወይም እርስዎን ሊገፋፉ ይችላሉ፡፡ በመስኮት የመታወቂያ ወረቀት ያላቸው ስለመሆናቸውይመልከቱ፡፡ በርዎን በመክፈት ያለጥበቃ እንዳይያዙ፡፡

**ደረጃ 3**

መኮንኖቹ የመያዥያ ወረቀት ያላቸው ስለመሆኑ ይጠይቋቸው

*መኮንኖቹ የመያዥያ ወረቀት ያላቸው ከሆነ* → ደረጃ 4

**ደረጃ 4**

እርስዎ የመያዣ ወረቀቱን የማየት መብት አለዎት፡፡ መኮንኖቹ ወረቀቱን በበሩ ስር ወይም በመስኮት ላይ  እንዲያሳይዎት ይጠይቁ፡፡ ከዚያም የመያዣ ወረቀቱን ያንብቡ፡፡ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ካልያዘ የማያገለግል ነው (ገጽ 4 ትን ይመልከቱ)፡፡ መኮንኖቹ ወደቤትዎ መግባት አይችሉም፡፡

**ደረጃ 5**

በማያገለግል የመያዣ ወረቀት በመያዝም ሆነ ባለመያዝ መኮንኖቹ ወደ ቤትዎ ከገቡ በቤትዎ ውስጥ ህጻናት፣ አረጋውያን ወይም የታመሙ ሰዎች መኖራቸውን ይንገሩዋቸው፡፡ ከሚያገለግል መያዣ ሳይዙ ወደቤትዎ ከገቡ፣ እርስዎ አለመስማማትዎን ይንገሩዋቸው፡፡ በጥብቅ ትኩረት መስጠት አለብዎት፡፡ ቤትዎን ለቀው ከሄዱ በኋላ የተከሰተውን በዝዝርዝር ይጻፉ፡፡ የመኮንኖቹን አይነት፣ ስማቸውን፣ የባጅ ቁጥራቸውን እና ማንኛውም ምስክር/ ምስክሮች የሚገኙበትን መረጃ በዝርዝር ያጠቃሉ፡፡  የመታወቂያ ወረቀት ይጠይቁ፡፡

*መኮንኖቹ የመያዥያ ወረቀት የሌላቸው ከሆነ* → ደረጃ 4

**ደረጃ 4**

መኮንኖቹ የመያዣ ወረቀት የሌላቸው ከሆነ ወደቤትዎ ለመግባት መብት የላቸውም፡፡ እርስዎ ቤትዎን እንዲለቁሎት መጠየቅይችላሉ፡

# የመያዣ ወረቀትን ስለማንበብ


## የመያዣ ወረቀትን እንዴት ያነቡታል

- መኮንኖቹ ወደ ስራ ቦታዎ ወይም ወደ ቤትዎ መግባት የሚችሉት 1. የሚያገለግል የመያዣ ወረቀት በመያዝ ወይም 2. የርስዎን ፈቃድ በማግኘት ወይም የአሰሪዎን ፈቃድ በማግኘት ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ (የሚያገለግል ማለት የመያዣ ወረቀቱ በሚመለከታቸው ባለስልጣናት የተሰጠ እና ግዴታ መከበር ያለበት ወረቀት ማለት ነው)፡፡
- የመያዣ ወረቀት የሚያገለግል እንዲሆን አንዳንድ መረጃዎችን ግዴታ መያዝ ይኖርበታል፡፡
- እባክዎ ከዚህ በታች የተቀመጡትን የተለያዩ አይነት የመያዣ ወረቀቶችን እና የሚያገለግሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የግድ መያዝ ያለባቸውን መረጃዎች ይመልከቱ፡፡
- እንደያሉበት ክፍለ ግዛት ወይም ቦታ የመያዣ ወረቀቶቹ የተለያዩ ገጽታ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ይህ ማለት የመያዣ ወረቀቶቹ የሚያገለግሉ ስለመሆናቸው በተለያዩ ትእዛዞች ወይም ከዚህ በታች ከተቀመጡት ናሙናዎች የተለዩ ሊመስሉ ይችላሉ፡፡
- መኮንኖቹ ለመግባት ፈቃድ ካላቸው እና መያዣ ከሌላቸው ወይም የሚያገለግል መያዣ ከሌላቸው እርስዎ ቤትዎን እንዲለቁ የመጠየቅ መብት ይኖርዎታል!

## የፍለጋ ወረቀት

የሚያገለግል የብርበራ ወረቀት:

- በዳኛ፣ በጸጥታ ፍትህ ወይም በአካባቢው ዳኛ የግድ ሊፈረም ይገባል፡፡
- የፍለጋውን አድራሻ የግድ መግለጽ ይኖርበታል፡፡
- ፍለጋው የሚካሄድባቸውን አካባቢዎች ግዴታ በዝርዝር መግለጽ ይኖርበታል፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች የፍለጋ ወረቀቶቹ የፍለጋ አካባቢዎችን በዝርዝር ለመግለጽ ይቻል ዘንድ ብዙ ረጃጅም ገጾች ሊኖሩዋቸው ይችላሉ፡፡
- የፍለጋ ወረቀቱን የማያገለግል ሊያደርጉ የሚችሉ ለምሳሌ ቀኑ ያለፈበት የፍለጋ ወረቀት ስለመሆናቸው ሌሎች መረጃዎችን የመልከቱ፡፡
- መኮንኑ የሚያገለግል የመያዣ ወረቀት ከሌለው ወይም ካልያዘ እርስዎ ለመናገር የሚችሉት "ይህ የሚያገለግል የመያዣ ወረቀት አይደለም፡፡ እርስዎ መግባት አይችሉም፡፡ እባክዎ ይልቀቁልኝ፡፡"
- መኮንኑ የሚያገለግል የመያዣ ወረቀት ካለው፣ ወደቤትዎ እንዲገቡ የግድ መፍቀድ ይኖርቦታል፡፡ በሚገቡበት ወቅትም ማለት ያለብዎ፣ ‹‹እኔ በዚህ ፍተሻ/ፍለጋ አልስማማም፡፡›› ይህ እነርሱ ለመፈተሽ የተፈቀደላቸውን ቦታ ውስጡን ያደርገዋል፡፡
- መኮንኖቹ ፍተሻውን የሚያደርጉባቸውን አካባቢዎች/ቦታዎች ላይ ምልከታ ያድርጉ፡፡ የፍተሻ/ፍለጋ ወረቀቱ የማይዘረዝራቸውን አካባቢዎች/ቦታዎች ይመልከቱ፡፡ ድጋሚ ከፍተሻው ጋር የማይስማሙ መሆንዎትን ይግለጹ፡፡ መኮንኑ ማንኛውንም ንብረትዎን ከወሰደብዎት ደረሰኝ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ፡፡



SW No. ________

STATE OF CALIFORNIA - COUNTY OF LOS ANGELES
SEARCH WARRANT AND AFFIDAVIT
(AFFIDAVIT)

[redacted]______________, swears under oath that the facts expressed by her in this Search
(Name of Affiant)
Warrant and Affidavit and in the attached and incorporated statement of probable cause are true and that based thereon she has probable cause to believe and does believe that the property and/or person described below is lawfully seizable pursuant to Penal Code Section 1524, as indicated below, and is now located at the locations set forth below. Wherefore, affiant requests that this Search Warrant be issued.

[redacted]______________, NIGHT SEARCH REQUESTED: YES [ ] NO [X]
(Signature of Affiant) HOBBS SEALING REQUESTED: YES[ ] NO [ ]

(SEARCH WARRANT)

THE PEOPLE OF THE STATE OF CALIFORNIA TO ANY SHERIFF, POLICE OFFICER OR PEACE OFFICER IN THE COUNTY OF LOS ANGELES: proof by affidavit having been made before me by [redacted]______,
(Name of County) (Name of Affiant)

that there is probable cause to believe that the property and/or person described herein may be found at the locations set forth herein and is lawfully seizable pursuant to Penal Code Section 1524 as indicated by "X"(s) in that:
_____ it was stolen or embezzled.
__X__ it was used as the means of committing a felony.
__X__ it is possessed by a person with the intent to use it as means of committing a public offense or is possessed by another to whom he or she may have delivered it for the purpose of concealing it or preventing its discovery.
__X__ it tends to show that a felony has been committed or that a particular person has committed a felony.
_____ it tends to show that sexual exploitation of a child, in violation of P.C. Section 311.3, or depiction of sexual conduct of a person under the age of 18 years, in violation of Section 311.11, has occurred or is occurring.
__X__ there is a warrant for the person's arrest;

YOU ARE THEREFORE COMMANDED TO SEARCH:

(See the attached description page 1 through 12 incorporated herein)

FOR THE FOLLOWING PROPERTY/PERSON:

(See the attached description page 1 through 12 incorporated herein)

AND TO SEIZE IT IF FOUND and bring it forthwith before me, or this court, at the courthouse of this court.
This Search Warrant and incorporated Affidavit was sworn to as true and subscribed before me this 1ST day of AUGUST, 2011, at 3:59 A.M./P.M. Wherefore, I find probable cause for the issuance of this Search Warrant and do issue it.

[redacted] [redacted]______________, NIGHT SEARCH APPROVED: YES [ ] NO [ x ]
(Signature of Magistrate)

Judge of the Superior Court, LOS ANGELES, CENTRAL Judicial District






ይህ መረጃ የቀረበው **በካቶሊክ ህጋዊ ኢሚግሬሽን ኔትወርክ አይኤንሲ** ነው፡፡ ለተጨማሪ መረጃ cliniclegal.org. ን ይጎብኙ፡፡

## የመያዣ ትእዛዝ ማንበብ

የሚያገለግል የብርበራ ወረቀት:

- በዳኛ፣ በጸጥታ ፍትህ ወይም በአካባቢው ዳኛ የግድ ሊፈረም ይገባል፡፡
- በቁጥጥር ስር የሚውለውን ወይም የሚያዘውን ግለሰብ ስም የግድ መጥቀስ ይኖርበታል፡፡
- የሚያዘውን ግለሰብ ዝርዝር መረጃ የግድ መጥቀስ ይኖርበታል፡፡
- የፍለጋ ወረቀቱን የማያገለግል ሊያደርጉ የሚችሉ ለምሳሌ ቀኑ ያለፈበት የፍለጋ ወረቀት ስለመሆናቸው ሌሎች መረጃዎችን የመልከቱ፡፡
- መኮንኑ የሚያገለግል የመያዣ ወረቀት ከሌለው ወይም ካልያዘ እርስዎ ለመናገር የሚችሉት “ይህ የሚያገለግል የመያዣ ወረቀት አይደለም፡፡ እርስዎ መግባት አይችሉም፡፡ እባክዎ ይልቀቁልኝ፡፡”
- መኮንኑ የሚያገለግል የመያዣ ትእዛዝ ከያዘ እና በመያዣ ትእዛዙ ላይ የተጠቀሰው ግለሰብ የሚገኝ ከሆነ ግለሰቡ ወደ ውጭ ወጥቶ መኮንኑን ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ከዚያም በሩን ዝጉት፡፡ በመያዣ ትእዛዙ ላይ በስም የተጠቀሰው ግለሰብ የሌለ ከሆነ ግለሰቡ በዚያ ቦታ እንደማይገኝ ለመኮንኑ ይንገሩት፡፡ እናም በሩን አይክፈቱት፡፡



WARRANT OF ARREST or CAPIAS – C.C.P., Arts. 15.01 – 15.02

IN JUSTICE COURT,

PRECINCT No. 3
of Williamson County

WARRANT OF ARREST

Cause No. 3FSW-14-[redacted]

Bond Amount $20,000.00
Fine & Cost Amount $______
Warrant Fee $______
total $______

THE STATE OF TEXAS
VS.
[redacted]

Address [redacted] City [redacted] State TX ZIP [redacted]

DOB [redacted] D.L. State TX D.L. # [redacted]

D.L. Expires none Social Security # [redacted] Other ID Info. ______

Race White Sex Male Height [redacted] Weight [redacted] Hair Brown Eyes Brown

THE STATE OF TEXAS

To any **PEACE OFFICER** of the State of Texas Greeting:

YOU ARE HEREBY COMMANDED to arrest [redacted] if to be found in the State of Texas, and bring him before me, a Justice of the Peace in and for Precinct No. 3 Of Williamson County, Texas, at my office in Georgetown, in said County immediately, to answer to the STATE OF TEXAS for an offense against the laws of said State to-wit: Manufacture or Delivery of a Controlled Substance in Penalty Group 1 less than 1 gram, to wit: Methamphetamine. HSC 481.112 (State Jail Felony) on or about August 1st, 2014 of which offense [redacted] is accused by the written complaint, under oath of [redacted] filed before me.

Herein Fail Not, but of this writ make due return, showing how you have executed the same.

Witness my official signature this 4th day of Dec A.D. 2014

[redacted] Justice of the Peace,

W.C.S.O. Case # [redacted] Precinct No. 3 Williamson County, Texas.

PEACE OFFICER RETURN

Came to hand the 5th day of Dec, A.D., 2014, at 0700 o'clock a M., and executed on the 5th day of Dec, A.D., 2014, at 0830 o'clock a M., by arresting the said Defendant at __________ in Williamson County, Texas, and * taking ______ bond, which is herewith returned; * placing him/her in the County jail of Williamson County, Texas. *(* Erase according to the facts.)*


I actually and necessarily traveled _____ miles in the service of this Writ, in addition to any other mileage I may have traveled in the service of other process in this cause during the same trip.

FEES – Executing/Processing Arrest Fee $______
Mileage ______ Miles ................ $______
Making Bond ................ $______
Commitment ................ $______
Release ................ $______
Total ................ $______

[redacted] Sheriff
[redacted] Williamson County, Texas
Peace Officer
(Law Enforcement Agency / Department)

## የመያዣ ትእዛዝ ስለማንሳት/ግለሰቡን ወደመጣበት አገር መመለስ (የኢሚግሬሽን ብርበራ ወረቀት)

- የመያዣ ትእዛዝ የሚነሳው ወይም ግለሰቡ ወደ መጣበት አገር ለመመለስ (የኢሚግሬሽን የመያዣ ወረቀት ለመኮንኑ ወደ ቤቱ እንዲገባ መብት አይሰጠውም፡፡ እንዲህ ይበሉ “በዚህ የብርበራ ወረቀት የመግባት መብት የሎትም፡፡ እባክዎ ይልቀቁልኝ”)



U.S. Department of Justice
Immigration and Naturalization Service

Warrant of Removal/Deportation

File No: __________

Date: __________

To any officer of the United States Immigration and Naturalization Service:

__________________________________________,
(Full name of alien)

who entered the United States at __________ on __________
(Place of entry) (Date of entry)

is subject to removal/deportation from the United States, based upon a final order by:

- [ ] an immigration judge in exclusion, deportation, or removal proceedings
- [ ] a district director or a district director's designated official
- [ ] the Board of Immigration Appeals
- [ ] a United States District or Magistrate Court Judge

and pursuant to the following provisions of the Immigration and Nationality Act:
Section 241(a)(5) of the Immigration and Nationality Act(Act), as amended.

I, the undersigned officer of the United States, by virtue of the power and authority vested in the Attorney General under the laws of the United States and by his or her direction, command you to take into custody and remove from the United States the above-named alien, pursuant to law, at the expense of the appropriation. "Salaries and Expenses Immigration and Naturalization Service 2002," including the expense of an attendant if necessary.

__________
(Signature of INS official)

__________
(Title of INS official)

__________
(Date and office location)

Form I-205 (Rev. 4-1-97)N




# የት ቦታ፡ በመንገድ ወይም በህዝብ መሰብሰቢያ አካባቢ

## ምን ማወቅ ያስፈልጎታል:

- ፖሊስ ወይም የኢሚግሬሽን ባለሙያዎች ወደ እርስዎ በመጠጋት ላይ መሆናቸውን ካዩ አለመሮጥ
- በመንገድ ላይ ከቆሙ ወይም በህዝብ መሰብሰቢያ አካባቢ ከቆሙ፣ ዝም የማለት እና ጥያቄዎችን ላለመመለስ መብት ይኖርዎታል፡፡
- በአንዳንድ ክፍለ ግዛቶች ህጉ እንደሚለው ፖሊሶች ስምዎን ከጠየቁ የግድ መንገር ይኖርቦታል፡፡ በገጽ 14 ላይ የተጠቀሱትን የድንገተኛ ግዜ እቅድ ለተጨማሪ መረጃ ይመልከቱ እና ለእርስዎ የላቀ የሚሆነውን እቅድ ይውሰዱ፡፡
- በአጠቃላይ አንድ መኮንን እርስዎን በቁጥጥር ስር ለማዋል የመያዣ ትእዛዝ ያስፈልጎታል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች መኮንኑ እርስዎን በቁጥጥር ስር ለማዋል የመያዣ ትእዛዝ የሚያስፈልገው እርስዎ ህጋዊ ካልሆኑ ወይም ወንጀል የፈጸሙ ከሆነ ነው፡፡
- በአንዳንድ ሁኔታዎች መኮንኖች እርስዎን የመበርበር መብት የሚኖራቸው እርስዎ የጦር መሳሪያዎችን ወይም ያልተፈቀዱ መሳሪያዎችን ወይም እቃዎችን የያዙ መሆንዎትን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ወቅት አይቃወሙ ወይም አይጣሉ፡፡
- እርስዎ በአውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ጠረፍ ላይ የሚገኙ ከሆነ ጥያቄ ሊቀርብልዎ የሚችል መሆኑን ወይም ያለ መያዣ በቁጥጥር ስር ሊውሉ የሚችሉ መሆኖትን ይወቁ፡፡ በዚህ ወቅትም ምንም ላለመናገር መብት ይኖርዎታል፡፡
- ባለፉት ጊዜያት የኢሚግሬሽን ባለሙያዎች/መኮንኖች በአንዳንድ የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ት/ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ የጸሎት ቦታዎችን፣ የቀብር ቦታዎችን፣ የጋብቻ ስነ ስርአት መፈጸሚያ ቦታዎችን፣ የህዝብ ሃይማኖታዊ ስነ ስርአቶች ወይም በህዝብ ሰላማዊ ሰልፎች (ለምሳሌ በማርሽ፣ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ወይም በመሳሰሉት) ሰዎችን በቁጥጥር ስር አያውሉም ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ወደፊት ሊቀየር ይችላል፡፡ በተጨማሪም እርስዎም እንዲህ ካሉት አካባቢዎች ከመድረስዎ በፊት እንዲቆሙ ወይም ወደ እነዚህ አካባቢዎች እንዳይገቡ ሊከለከሉ ይችላሉ፡፡

## ምን ማድረግ አለብን:

### ደረጃ 1

ምንም ነገር ከመናገርዎ በፊት ስምዎን ጨምሮ እኔ እንድሄድ እና እንዴት ይፈቀድልኛልን? በማለት ይጠይቁ በከፍተኛ ድምጽ ማለት ያለብዎ እርስዎ ምንም

### ደረጃ 2

መኮንኑ አዎን የሚል መልስ ከሰጠዎት፤ ቀስ በማለት ወይም በዝግታ ይራመዱ፡፡ መኮንኑ አይ ካለ ግን ከዚያ አካባቢ አይንቀሳቀሱ

### ደረጃ 3

ዝም የማለት መብት አለዎት፡፡ ስለ ኢሚግሬሽን ሁኔታዎ የት እንደተወለዱ፣ ወይም ወደ ዩናይትድ ስቴት መቼ እንደገቡ ምንም አይነት መረጃ አይስጡ፡፡ ከትውልድ አገርዎ ይዘው የመጡትን ማናቸውንም አይነት ሰነዶች አያሳዩ፡፡ መናገር እንደማይፈልጉ ወይም እርስዎ ስለመብትዎ የሚያውቁ መሆኖትን እና ካርዶን ያሳዩ

### ደረጃ 4

“መኮንኑ የሚበረብሮት፣ በቁጥጥር ስር የሚያውሎት ከሆነ ይረጋጉ፡፡ አይቃወሙት ወይም ግብ ግብ ወይም ድብድብ አይያያዙ የሚበረበሩ ከሆነ እኔ ለብርበራው አልስማማም ይበሉ፡፡”


ይህ መረጃ የቀረበው በካቶሊክ ህጋዊ ኢሚግሬሽን ኔትወርክ አይኤንሲ ነው፡፡ ለተጨማሪ መረጃ cliniclegal.org. ን ይጎብኙ፡፡



# የት ቦታ፡ በስራ ቦታዎ

## ምን ማወቅ ይፈልጋሉ:

- ወደ ስራ ቦታዎ ለመግባት የኢሚግሬሽን መኮንኖቹ ወይም ፖሊሱ መያዝ ያለባቸው 1 የሚያገለግል የመያዣ ወይም 2 የአሰሪዎን ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል፡፡
- አይሩጡ፡፡ የሚሮጡ ከሆነ እርስዎ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ወይም እንዲያዙ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- የመያዣ/የመበርበሪያ ወረቀቱን ማሳየት ማለት እርስዎ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይደረጋሉ ማለት አይደለም፡፡
- የኢሚግሬሽን ወይም የፖሊስ መኮንኖች ጥያቄ የሚያቀርቡልዎ ከሆነና እርስዎ ዝም ማለትን የመረጡ ከሆነ፤ በከፍተኛ ድምጽ ምንም መናገር አለመፈለግዎን ወይም ለመኮንኖቹ መብትዎን የሚያውቁ መሆንዎትን የሚያስረዳ የመብትዎን ካርድ ያሳዩ
- በገጽ 18 ላይ ያለውን የስራ ቦታ ዝርዝር/፤ ቼክሊስት መሙላትዎን ያረጋግጡ

## ምን ማድረግ አለብን:

**ደረጃ 1**

ከስራ ባልደረባዎ ጋር ድንገተኛ ፍተሻ ወቅት የድንገተኛ ጊዜ እቅድ ሲሆን ያለዎት መሆኑን ያረጋግጡ ስለመሆኑ ማስታወስ ያለብዎ እርስዎን የመሸወድ፣ ወይም ማስፈራራት ይችላሉ፡፡

**ደረጃ 2**

አሰሪዎ በቦታው ካልተገኙ ወይም  አሰሪዎ እንዲገቡ ከፈቀዱ መኮንኖቹ የሚያነጋግሩዋቸውን አንድ ግለሰብ በመምረጥ መኮንኖቹን እንዲህ ባሉት ድንገተኛ የፍተሻ ጊዜያት መታወቂያቸውን እንዲጠይቋቸው ያድርጉ

**ደረጃ 3**

ግለሰቡ የመጥሪያ ወረቀቱን በጥንቃቄ በማንበብ እና ጊዜው ያላለፈበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ኦፊሰሮች ለማዕበርበር ጫና ሊፈጥሩብህ ወይም ሊያስፈራሩህ ይችላሉ፡፡

**ደረጃ 4**

ሁኔታዎ የት እንደተወለዱ፣ ወይም ወደ ዩናይትድ ስቴት መች እና እንዴት እንደገቡ ምንም አይነት መረጃ አይስጡ፡፡ ከትውልድ አገርዎ ይዘው የመጡትን ማናቸውንም አይነት ሰነዶች አያሳዩ፡፡ በከፍተኛ ድምጽ ማለት ያለብዎ እርስዎ ምንም መናገር እንደማይፈልጉ ወይም እርስዎ ስለመብትዎ የሚያውቁ መሆኖትን እና ካርዶን ያሳዩ

**ደረጃ 5**

ኦፊሰሩ ከፈተሸ፣ ካሰረህ ወይም በቁጥጥር ስር ካዋለህ በተረጋጋ ሁኔታ መቆየት አለብህ እንጂ ፀብ መፍጠር የለብህም ከተፈተሸክ በጥሞና ይህ ፍተሻ እንዲካሄድብኝ አልፈልግም በላቸው



# የት ቦታ፡ የእርስዎ ተሽከርካሪ ውስጥ

## እርስዎ ማወቅ የሚገባዎት ነገር፡

- እርስዎ መኪናዎን እያሽከረከሩ ባሉበት ሁኔታ አውራ ጎዳናው ላይ በሚቆሙበት ጊዜ ልዩ ልዩ ህጎች በእርስዎ ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡
- እርስዎ በድንበር መቆጣጠሪያ ኬላ ላይ መኪናዎን እንዲያቆሙ ከተደረገ የድንበር ተቆጣጣሪዎች መኪናዎትን ሊፈትሹ ይችላሉ፡፡

## ምን ማድረግ አለብን:

### ደረጃ 1

መኪናዎትን በማቆም ሞተርዎን ያጥፉ፡፡ የኮፈኑን መብራት ያብሩ፡፡ እጅዎትን የድንበር ተቆጣጣሪዎቹ ሊያዩት በሚችሉበት መልኩ የመኪናው መሪ ላይ ያኑሩ፡፡

### ደረጃ 2

ጥያቄ በቀረበልዎ ጊዜ የድንበር ተቆጣጣሪ ሠራተኛዎ የሚሰጥዎትን ትዕዛዝ በመከተል የመንጃ ፈቃድዎን፣ የተሽከርካሪ ምዝገባ ሰነድ እና የመድህን ዋስትና ማረጋገጫዎችን ማሳየት ይኖርብዎታል፡፡ እርስዎ የመንጃ ፈቃድ ወይም የተሽከርካሪ ምዝገባ ሰነድ ካልያዙ ሃሰተኛ ሰነድ መስጠት ወይም የውሸት መግለጫ መስጠት አይኖርብዎትም

### ደረጃ 3

የድንበር ተቆጣጣሪ ሠራተኛው መኪናዎትን መፈተሽ እንደሚፈልግ ሲነግርዎት “እኔ ፈቃደኛ አይደለሁም” ብለው መልስ መስጠት ይችላሉ፡፡ በአንድ አንድ አጋጣሚዎች ይህ የድንበር ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ያለ እርስዎ ፈቃድ ወይም ምንም አይነት ዋስትና ሳይሰጥዎት ፍተሻ ሊያከናውን ይችላል፡፡ ያም ሆኖ እርስዎ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ መናገር ይችላሉ፡፡

### ደረጃ 4

ምንም ሳይናገሩ ዝም ብለው የመቆየት መብትዎ የተጠበቀ ነው፡፡ ስለእርስዎ የስደተኝነት ሁኔታ በተመለከተ ማለትም የትውልድ ቦታዎን፣ ወይም ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የገቡበትን ጊዜ በተመለከተ ማንኛውንም አይነት መረጃ መስጠት አይጠበቅብዎትም፡፡ ከትውልድ ሃገርዎ የተሰጠዎትን ማንኛውንም አይነት ሰነድ ለባለሙያው ማሳየት አይጠበቅብዎትም፡፡ እርስዎ ምንም አይነት መረጃ መስጠት እንደማይፈልጉ በመግለፅ ድምፅዎን ጎላ አድርገው ከተናገሩ ግለሰቡ ይህንን መብትዎን ስለሚረዳ ያከብርልዎታል፡፡



ይህ መረጃ የቀረበው በካቶሊክ ህጋዊ ኢሚግሬሽን ኔትወርክ አይኤንሲ ነው፡፡ ለተጨማሪ መረጃ cliniclegal.org. ን ይጎብኙ፡፡



# የት ቦታ፡ በፖሊስ እስር ቤት/ማረፊያ ቤት ውስጥ

## እርስዎ ማወቅ የሚገባዎት ነገር፡

- እስር፣ ክስ እና በፍርድ ቤት የወንጀለኛነት ማረጋገጫ ውሳኔ ከተላለፈ የእርስዎ የስደተኝነት ሁኔታ ላይ ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡
- እርስዎ ወደመጡበት ሃገር እንዲመለሱ ሊደረጉ የሚችሉበት አስገዳጅ ሁኔታ ከተከሰተ ከፖሊሱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ከማድረግ መቆጠብ ይኖርብዎታል፡፡
- ስልክ የመደወል መብትዎ የተጠበቀ ነው፡፡
- ምንም አይነት ምላሽ ሳይሰጡ ዝም የማለት መብት አለዎት፡ ፡ እርስዎ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋሉ ወይም ታሰሩ ማለት ለቀረቡልዎት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል ማለት አይደለም፡፡
- ከጠበቃዎ ጋር የመነጋገር መብት አለዎት፡፡ ጠበቃ እንዲጠራልዎ በመጠየቅ የማግኘት መብት አለዎት
- ከጠበቃዎ ጋር ከመነጋገርዎ በፊት ምንም አይነት ሰነድ ላይ አልፈርምም ብለው መቃወም ይችላሉ፡፡
- እርስዎ ከፖሊሱ ጋር እየተነጋገሩ ባሉበት ወቅት ከጠበቃዎ ውጪ ከማንም ግለሰብ ጋር በመነጋገር መረጃ ልውውጥ ማድረግ የለብዎትም፡፡ ይህም የሚያካትተው ስለ ትውልድ ሃገርዎ፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዴት እና መቼ እንደመጡ ወይም ስለ ህክምና ታሪክዎ በተመለከተ ሊሆን ይችላል፡፡ እርስዎ ምንም አይነት መረጃ መስጠት እንደማይፈልጉ በመግለፅ ድምፅዎን ጎላ አድርገው ከተናገሩ ግለሰቡ ይህንን መብትዎን ስለሚረዳ ያከብርልዎታል፡፡
- በአንድ አንድ አጋጣሚዎች የፖሊስ አባሉ ከኢሚግሬሽን ባለስልጣን ኃላፊዎች ጋር በስልክ ለመወያየት ወይም እርስዎን አሳልፎ ለእነዚህ ባለስልጣን ወገኖች ሊያስረክብዎት ይችላል፡፡ ስለሆነም ከጠበቃዎ ውጪ ምንም አይነት መረጃ ለሌላ ግለሰብ መግለፅ የለብዎትም የሚባለው ለዚህ ነው፡፡
- ከጠበቃዎት ጋር በሚገናኙበት ጊዜ ስለ ስደተኝነት ሁኔታዎ እና ከዚህ በፊት ስለነበርዎ የወንጀለኝነት ታሪክ በግለፅ መናገር ይኖርብዎታል፡፡

## ምን ማድረግ አለብን:

**ደረጃ 1**

ስልክ መደወል እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ለቅርብ ተጠሪዎ መደወል ይችላሉ፡፡ (የቤተሰብ አባል፣ ጠበቃ፣ የቤተ እምነት ወይም ማህበር፣ ህግ አማካሪ ሊሆን ይችላል፡፡) (ለአስቸኳይ/አደጋ ጊዜ የሚደውሉለትን ግለሰብ በተመለከተ ገጽ 14 ላይ የሰፈረውን ይመልከቱ)

**ደረጃ 2**

የስደተኝት ሁኔታዎን በተመለከተ ከጠበቃዎ ውጪ ላለ ሌላ ማንኛውም ግለሰብ ጋር ውይይት አያድርጉ፡፡ ይህ የሚያካትተው የትውልድ ሃገርዎን፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዴት እንደመጡ ወይም የቀድሞ የወንጀል ታሪክዎን በተመለከተ ሊሆን ይችላል፡፡ እርስዎ ምንም አይነት መረጃ መስጠት እንደማይፈልጉ በመግለፅ ድምፅዎን ጎላ አድርገው ከተናገሩ ግለሰቡ ይህንን መብትዎን ስለሚረዳ ያከብርልዎታል፡፡ እርስዎ የሚናገሩት ማኛውም መግለጫ በእርስዎ ላይ እንደማስረጃ ሊወሰድብዎት ይችላል፡፡

**ደረጃ 3**

ከጠበቃዎ ጋር ሳይነጋገሩ በፊት ምንም አይነት ሰነድ አይፈርሙ፡፡ የሆነ ሰነድ አቅርበው እንዲፈርሙ ከተጠየቁ "ጠበቃዬ በሌለበት ምንም አይነት ሰነድ አልፈርምም" ማለት ይችላሉ፡፡ ስለቀረበልዎት ጥያቄ ወይም እንዲፈርሙ ስለተጠየቁት ሰነድ አስመልክቶ ግልፅ ካልሆነልዎት ማብራሪያ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**ደረጃ 4**

ጠበቃዎ ከእርስዎ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሰጡትን ሰነዶች በጠቅላላ የፎቶ ኮፒ ቅጂ አድርገው መያዝዎትን ያረጋግጡ፡፡




# የት ቦታ፡ በኢሚግሬሽን ጊዜያዊ የእስረኛ ማቆያ ማዕከል

## እርስዎ ማወቅ የሚገባዎት ነገር፡

- ስልክ የመደወል መብትዎ የተጠበቀ ነው፡፡
- ወደ ህግ አማካሪዎ ስልክ የመደወል መብት አለዎት፡፡
- ምንም ነገር ሳይናገሩ ዝም የማለት መብት አለዎት፡፡ በቁጥጥር ስር ዋሉ ማለት ግን ለቀረበልዎት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል ማለት አይደለም፡፡
- ከጠበቃዎ ወይም ህጋዊ እውቅና ከተሰጠው ተወካይዎ ጋር የመነጋገር መብት አለዎት፡፡ እርስዎ ወይም የእርስዎ የቤተሰብ አባል የሆነ ግለሰብ ከጠበቃዎ ወይም ህጋዊ እውቅና ከተሰጠው ተወካይዎ ጋር በመገናኘት የመነጋገር መብት አላችሁ፡፡ ይህ እንዲቀርብልዎት በጠየቁበት ቅፅበት ይሟላልዎታል፡፡
- ከጠበቃዎ ወይም ህጋዊ ተወካይዎ ጋር ሳይነጋገሩ በፊት ምንም አይነት ሰነድ አልፈርምም ማለት ይችላሉ፡፡
- ጠበቃዎ ወይም ህጋዊ ወኪልዎን በሚያነጋግሩበት ወቅት ከዚህ ቀደም ስለነበረ እስር ወይም የወንጀለኛነት ህግዎ በግልፅ መናገር የሚያስፈልግ ሲሆን ይህ መግለጫ ከእርስዎ መረጃ እንደተሰረዘ ሌላ ግለሰብ የነገረዎት ቢሆንም እንኳን እውነቱን መግለፅ ይኖርብዎታል፡፡
- ወደመጣበት ሃገር የመመለስ ስጋት የተጋረጠበት ማንኛውም ግለሰብ ጊዜያዊ የእስር ማዕከል ዘንድ በመሄድ እስረኛ መጠየቅ ወይም ከኢሚግሬሽን ባለስልጣኖች ጋር በፈቃደኝነት መነጋገር አይኖርበትም፡፡

## ምን ማድረግ አለብን:

**ደረጃ 1**

ስልክ መደወል እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ለቅርብ ተጠሪዎ መደወል ይችላሉ፡፡ (የቤተሰብ አባል፣ ጠበቃ፣ የቤተ እምነት ወይም ማህበር፣ ህግ አማካሪ ሊሆን ይችላል፡፡) (ለአስቸኳይ/አደጋ ጊዜ የሚደውሉለትን ግለሰብ በተመለከተ ገጽ 14 ላይ የሰፈረውን ይመልከቱ)

**ደረጃ 2**

ወደ ህግ አማካሪው በመደወል እገዛ መጠየቅ ይችላል፡፡

**ደረጃ 3**

የስደተኝት ሁኔታዎን በተመለከተ ከጠበቃዎ ውጪ ላለ ሌላ ማንኛውም ግለሰብ ጋር ውይይት አያድርጉ፡፡ ይህ የሚያካትተው የትውልድ ሃገርዎን፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዴት እንደመጡ ወይም የቀድሞ የወንጀል ታሪክዎን በተመለከተ ሊሆን ይችላል፡፡ እርስዎ ምንም አይነት መረጃ መስጠት እንደማይፈልጉ በመግለፅ ድምፅዎን ጎላ አድርገው ከተናገሩ ግለሰቡ ይህንን መብትዎን ስለሚረዳ ያከብርልዎታል፡፡ እርስዎ የሚናገሩት ማኛውም መግለጫ በእርስዎ ላይ እንደማስረጃ ሊወሰድብዎት ይችላል፡፡

**ደረጃ 4**

ከጠበቃዎ ወይም ህጋዊ ተወካይዎ ጋር ሳይነጋገሩ በፊት ምንም አይነት ሰነድ አልፈርምም ማለት ይችላሉ፡፡

የሆነ ሰነድ አቅርበው እንዲፈርሙ ከተጠየቁ "ጠበቃዬ በሌለበት ምንም አይነት ሰነድ አልፈርምም" ማለት ይችላሉ፡፡ ስለቀረበልዎት ጥያቄ ወይም እንዲፈርሙ ስለተጠየቁት ሰነድ አስመልክቶ ግልፅ ካልሆነልዎት ማብራሪያ መጠየቅ ይችላሉ፡፡


ይህ መረጃ የቀረበው በካቶሊክ ህጋዊ ኢሚግሬሽን ኔትወርክ አይኤንሲ ነው፡፡ ለተጨማሪ መረጃ cliniclegal.org. ን ይጎብኙ፡፡

# በየትኛውም ሁኔታ ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ማስታወስ የሚገባዎ አስራ ሁለት ነገሮች


1. የምትናገው ነገር አንተን ለመጉዳት ሊውል ይችላል፡፡

2. ዝም ለማለት መብት አለዎት፡፡



3. ዝም ማለት ከፈለጉ ከፍ ብሎ ዝም እንዲሉ ይናገሩ ወይም የመብቶች ካርድዎትን ከፍ አድርገው ያሳዩ፡፡

አንደኛውን በገጽ 13 ላይ ያሉ




4. ሁልጊዜ የአሜሪካ መታወቂያ እና የስደት ግልባጭ ሰነዶችን ይዘው ይንቀሳቀሱ፡፡

5. ሀሰተኛ ሰነዶችን ወይም የሌላ ሃገር ሰነዶችን በፍፁም ይዘው አይንቀሳቀሱ፡፡

6. ሀላፊዎችን ፈጽሞ አይዋሹ፡፡

7. ከጠበቃዎ ጋር ለመነጋገር መብት አለዎት፡፡

8. በፍፁም በተከለከለ ነገር መንገድ አይሩጡ ወይም በባለስልጣኖች በታዘዙ ኢያድርጉት፡፡



9. ከታሰሩ ወይም ከተያዙ በፍፁም የአካላዊ ጥል እንዳያካሄዱ፡፡



10. ከጠበቃዎ ጋር ከመነጋገርዎ በፊት ምንም አይነት ነገር ላለመፈረም መቃወም ይችላሉ፡፡



11. በፖሊስ ጥበቃ ስር ካሉ ወይም ካገደው ካሉ የስደት መረጃዎችን ወይም የወንጀል ታሪክዎትን ከጠበቃ ውጪ ከማንም ጋር እንዳይወያዩ፡፡

12. ጥያቄ ካለዎት ወይም ያልገባዎት ነገር ካለ ምቹ ጊዜ እንዳገኙ ምን እንደተፈጠ ይጻፉ፡፡ ወዲያውኑ ለጠበቃው እና ለደጋፊ ቡድኖ ይናገሩ፡፡

# የቦታ መምሪያ



## እቤት ውስጥ

- በሩን አትክፈቱ:: የመታወቂያ ይጠየቁ (በመስኮት በኩል)::
- ኃላፊዎች ብቻ በህጋዊ ወረቀት ወይም በእርሶ ፈቃድ ሊገቡ ይችላሉ::
- የፈቃድ ወረቀት እንዲያሳዩ ይጠየቁ:: ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ኃላፊዎች እንዲወጡ ይጠይቁ::
- ኃላፊዎች (በህጋዊ ወይም ህጋዊ ባልሆነ ወረቀት) እርስዎ መግባታቸውን እንዳልፈቀዱ እየተናገራችኋቸው ከገቡ ልጆች፣ ሽማግሌዎች ወይም የታመሙ ሰዎች እቤት ውስጥ ካሉ ይህንን ጉዳይ ይንገሯቸው::





## መንገድ ላይ/የህዝብ ማመላለሻ ቦታ

- አይሩጡ::
- እንዳይሮጡ፣ ምንም ከመናገርዎ በፊት (ስምዎትን ጨምሮ) መሄድ እችላለሁ ብለው ይጠይቁ?
- አዎ ከሆነ በዝግታ ለመሄድ ይራመዱ፣ አይ ከሆነ አይራመዱ::
- በጥቂት ሃገራት ውስጥ ስምዎትን መስጠት ይኖርብዎታል::
- የሚፈለጉ ከሆነ በእርጋታ ይቀመጡ እና በመፈለጌ ላይ አልስማማም ይበሉ::



## የስራ ቦታ

- ኃላፊዎች ብቻ ተቀባይነት ባለው ህጋዊ ወረቀት ወይም በአሰሪዎ ፈቃድ ሊገቡ ይችላሉ::
- ከስራ ባልደረባቸው ጋር የአደጋ ጊዜ እቅድ ይኑርዎ (ገጽ 18ን ይመልከቱ)::
- አሰሪዎ ከሌለ ወይም ኃላፊዎች እንዲገቡ ከፈቀደ ኃላፊዎቹን የሚያነጋግረው ማን እንደሆነ ይወቁ:: ጠያቂው መታወቂያ እና የመግቢያ ወረቀት መጠየቅ ይኖርበታል::
- የሚፈለጉ ከሆነ በእርጋታ ይቀመጡ እና በመፈለጌ ላይ አልስማማም ይበሉ::



## መኪና ውስጥ

- ሂሳቡን እንዲሁም የመኪናውን ሞተር ከዚያ እጅዎትን በመሪው ላይ ያስቀምጡ::
- የመንጃ ፈቃድን፣ የምዝገባ ወረቀት እና የኢንሹራንስ ወረቀትን ማሳየት ሁሉንም ትእዛዞች የውሸት ሰነዶችን አያቅርቡ::
- ኃላፊው መኪናዎትን የሚፈለጉ ከሆነ በእርጋታ ይቀመጡ እና በዚህ ፍለጋ ላይ አልስማማም ይበሉ::



## እስር ቤት/ፖሊስ ጣቢያ

- ለጠበቃዎ ወይም ሌላ የአደጋ ጊዜ መገናኛዎ  ስልክ ለመደል ይጠይቁ::
- የመብቶች ካርድዎን ይጠቀሙ:: ዝም ለማለት እና ከጠበቃዎ ጋር ከመነጋገርዎ በፊት ምንም አይነት ነገር ላለመፈረም መብት ያለዎት መሆኑን ያስታውቁ::
- ከጉዳዩ ጋር በተገናኘ ያሉትን እና ጠበቃዎ ከዳኛው የሰጣቸውን ሰነዶች በሙሉ ግልባጭ ይጠይቁ::




## የስደተኛ መከላከያ ጣቢያ

- ለጠበቃዎ ወይም ሌላ የአደጋ ጊዜ መገናኛዎ እንዲሁም ለቆንስላዎ ስልክ ለመደል ይጠይቁ::
- የመብቶች ካርድዎን ይጠቀሙ:: ዝም ለማለት እና ከጠበቃዎ ጋር ከመነጋገርዎ በፊት ምንም አይነት ነገር ላለመፈረም መብት ያለዎት መሆኑን ያስታውቁ::
- ከጉዳዩ ጋር በተገናኘ ያሉትን ሰነዶች በሙሉ ግልባጭ ይጠይቁ::
- በቦንድ ለመለቀቅ ይጠይቁ::


ይህ መረጃ የቀረበው በካቶሊክ ህጋዊ ኢሚግሬሽን ኔትወርክ አይኤንሲ ነው:: ለተጨማሪ መረጃ cliniclegal.org. ን ይጎብኙ::

# የመብትዎን ይወቁ የሚል ካርድ

**መብቶዎን ይወቁ የሚል ካርድን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የሚፈስጡ ትእዛዞች**

1. የካርዱን ሁለት ግልባጮች ይቁረጡ፣ በግማሽ ይጠፉ፡፡
2. በሁለቱም ካርዶች ላይ የጠበቃዎትን የስልክ ቁጥር ያረጋግጡ፡፡
3. ሁልጊዜ ሁለቱንም የተሞሉ ካርዶች ከእርሶ ጋር ይያዙ፡፡ ይሄንን ካርድ ለስደት ሀላፊዎች ወይም ፖሊሲ ካሳዩ ይወስዱብሃል እንዲሁም አይመልሱም፡፡ ሁልጊዜ የካርዶቹን ሁለት ግልባጮች መያዝ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው፡፡
4. በስደት ኃላፊዎች ወይም ፖሊስ ጥቃት ወይም ያለአግባብ ጣልቃ መግባት በሚፈጠርበት ጊዜ መብትዎትን የሚያስታውስዎት እና እነዚህን ካርዶች ያሳዩ፡፡
5. በዚህ ካርድ ፊትለፊት ላይ እርስዎ ዝም ለማለት ያለዎትን መብት የመጠቀም ሁኔታ የሚገልፁ ናቸው፡፡ ከስደት ሀላፊዎች ጋር ወይም ከፖሊሱ ጋር ከተጋጩ የሚናገሩት ነገር በእርስዎ ላይ እንደሚያዝ ያስታውሱ፡፡ ዝም የማለት መብት አለዎት፡፡ ዝም የማለት መብትዎን የመጠቀም ለሃላፊዎቹ ይሄንን የካርድ ግልባጭ ያሳዩ ወይም በዛ ላይ ያለውን ዓ/ነገር ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡ፡፡ ያለውን ዓረፍተ ነገር ቃለ በቃል መናገር የማያስፈልገው ከሆነ ደግሞ ዝም የማለት መብትዎን እየተጠቀሙ እንደሆነ መግለጽ ይኖርብዎታል፡፡
6. በካርዱ ጀርባ ላይ የመብትዎን ዝርዝር ያገኛሉ፡፡ ሁልጊዜም እነዚህን ያንብቧቸው፣ ዝግጁ ይሁኑ፡፡
7. እራስዎን ለመከላከል በካርዱ ላይ የተመከተውን መረጃ በደንብ ይረዱ፡፡

**ዝም ማለት መብቴን እየተጠቀምኩ ነው፡፡**

ጸጥ ብሎ የመቆየት መብቴን ለመጠቀም እየመረጥኩ መሆኔን እባክዎትን ይወቁ። በተጨማሪም ጠበቃዬ እስኪያየው ድረስ ማንኛውንም ነገር ያለመፈረም መብቴን እየተጠቀምኩ ነው። ከታሰርኩ፣ ጠበቃዬን ወዲያውኑ እንዲያገኙ እጠይቃለሁ። የጠበቃዬ መገኛ አድራሻ ይህ ነው፥.

ስም ____________________

ስልክ ቁጥር ____________________

የታጠፈው

**ይሄንን አውቃለሁ፡፡**

1. መብቶች አሉኝ፡፡ ክብር አለኝ፣ ብቻዬን አይደለሁም፡፡
2. ጠበቃዬን የማናገር መብት አለኝ፡፡
3. ጠበቃዬ በክለሳ እስከምመለከታቸው ድረስ ማንኛውም ጉዳይ ያለመፈረም መብት አለኝ
4. የተናገርኩት ነገር በእኔ ላይ ሊያዝብኝ ይችላል፡፡
5. በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ዝም ለማለት መብት አለኝ፡፡
6. ዝም እላለሁ የሚለውን ለሀላፊዎች ለመግለጽ ይሄንን ካርድ አሳያለሁ ወይም ድምጼን ከፍ አድርጌ እናገራለሁ፡፡

**ዝም ማለት መብቴን እየተጠቀምኩ ነው፡፡**

ጸጥ ብሎ የመቆየት መብቴን ለመጠቀም እየመረጥኩ መሆኔን እባክዎትን ይወቁ። በተጨማሪም ጠበቃዬ እስኪያየው ድረስ ማንኛውንም ነገር ያለመፈረም መብቴን እየተጠቀምኩ ነው። ከታሰርኩ፣ ጠበቃዬን ወዲያውኑ እንዲያገኙ እጠይቃለሁ። የጠበቃዬ መገኛ አድራሻ ይህ ነው፥.

ስም ____________________

ስልክ ቁጥር ____________________

**ይሄንን አውቃለሁ፡፡**

1. መብቶች አሉኝ፡፡ ክብር አለኝ፣ ብቻዬን አይደለሁም፡፡
2. ጠበቃዬን የማናገር መብት አለኝ፡፡
3. ጠበቃዬ በክለሳ እስከምመለከታቸው ድረስ ማንኛውም ጉዳይ ያለመፈረም መብት አለኝ
4. የተናገርኩት ነገር በእኔ ላይ ሊያዝብኝ ይችላል፡፡
5. በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ዝም ለማለት መብት አለኝ፡፡
6. ዝም እላለሁ የሚለውን ለሀላፊዎች ለመግለጽ ይሄንን ካርድ አሳያለሁ ወይም ድምጼን ከፍ አድርጌ እናገራለሁ፡፡

# የአደጋ ጊዜ እቅድ መመሪያ

**የአደጋ እቅድ ለ፡** ______________________________

**በአደጋ ጊዜ ጠበቃዎቹ ወይም ጠበቃ ወይም እውቅና ያለው ተወካይ እንዲረዳዎ ያግኙ፡፡** ከጠበቃ ወይም እውቅና ካለው ተወካይ ጋር ለመነጋገር እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ግለሰቡ የሚረዳዎት መሆኑን ሳያረጋግጡ በፊት ስልክ ቁጥሩ አይጻፉ

ለሌላ የስደት ደረጃ **ህጋዊ መሆንዎትን ለማረጋገጥ በጠበቃ ወይም እውቅና** ባለው ተወካይ የሚደረግ ምልመላ ያግኙ፡፡

**በሃገር ውስጥ ቆንስላ ይመዝገቡ፡፡**

**ከቤተክርስርያንዎ፣ ከሰበካ ጉባኤዎ ወይም ሌሎች የሃይማኖት ወይም የማህበረሰብ ማእከላት ላይ ይመዝግቡ እና ግንኙነት ይፍጠሩ፡፡**

የቤተሰብ አባል በሚታሰርበት፣ በሚታደግበት ወይም በሚጣበት ወቅት ምን ማድረግ **እንዳለብዎ እቅድ ያውጡ፡፡**

- ለማን መደወል እንዳለበት እና በምን ትእዛዝ መደወል እንዳለበት ይወስኑ፡፡
- በጥቂት ሃገራት ውስጥ ህጎቹ ስሞትን ለፖሊሲ እንዲሰጡ ይፈልጋሉ፡፡ በሃገርዎ ውስጥ ስምዎትን መስጠት ያለብዎት እንደሆነ ይወቁ፡፡ ስምዎትን ከተጠየቁ ምን ማድረግ እንዳለብዎ እቅድ ያውጡ፡፡ ስምዎትን አለመስጠት ሊያሳስርዎ ወይም ሊያሳግደው የሚችል መሆኑን ከግምት ያስገቡ፡፡ ስምዎትን አለመስጠት ቤተሰብዎ እርሶን በመከልከያ ቦታ ወይም በፖሊሲ ጥበቃ ቦታ እንዳያገኝዎ ያስቸግራቸዋል ወይም እንዳይችሉ ያደርጋል፡፡ በልዩ ሁኔታ ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ከጠበቃው ጋር ይነጋገሩ፡፡

**ለሁሉን የቤተሰብ አባላት የስደት ወረቀቶችን እና ሌሎች አስፈላጊ ወረቀቶችን ግልባጭ ያድርጉ፡፡ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጧቸው፡፡** እነዚህን ወረቀቶች የት እንዳስቀመጡ ማንም ታማኝ ጓደኛ፣ የቤተሰብ አባል ሆኖ ከእርስዎ ጋር የማይኖር ወይም የማህረሰቡ አባል እንደማያውቁ ያረጋግጡ ግልባጮቹንንም ይስጧቸው፡፡

*ጠቃሚ ወረቀቶች፦*

- የስራ ማረጋገጫ
- የመታወቂያ ግልባጮች
- ፓስፖርቶች
- ሌሎች ማናቸውም የስደት ወረቀቶች ግልባጮች ማለትም የደረሰኝ መግለጫዎች እና ሌሎች ጉዳዮች እንዲሁም የቤተሰብ ማመልከቻ የማረጋገጫ ማስታወቂያዎች፡፡
- የልደት የምስክር ወረቀቶች (ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ትርጉሞቻቸው ጋር)
- የጋብቻ የምስክር ወረቀቶች (ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ትርጉሞቻቸው ጋር)
- የማህበራዊ ደህንነት ካርዶች
- ከወንጀል እስራቶች ወይም ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች
- ባለፉት ጊዜያት እርስዎን የወከሉትን የጠበቃዎች ስምና የመገናኛ መረጃ፡፡
- ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ምሳሌ የቤተሰብ አባላት የሚወስዷቸው የመድሃኒቶች ዝርዝር


ይህ መረጃ የቀረበው በካቶሊክ ህጋዊ ኢሚግሬሽን ኔትወርክ አይኤንሲ ነው፡፡ ለተጨማሪ መረጃ cliniclegal.org. ን ይጎብኙ፡፡

**በአደጋ ጊዜ ልጆችዎን ማን እንደሚንከባከብ ይወስኑ፡፡** እንዲሁም ግለሰቡ ስለልጆችዎ በቂ መረጃ ያለው መሆኑን ያረጋግጡ፣ ይሄውም የሚያስፈልጋቸው የመድሃኒት አይነት፡፡ ማናቸውንም ህጋዊ ሰነዶች (የውክልና ስልጣን ማስረጃ የመሳሰሉ ወረቀቶችን) መፈረም ካለብዎ ማለትም በአደጋ ጊዜ የልጅዎችዎን ደህንት ለማረጋገጥ ይሄንን መፈረም ካለብዎ ጉዳዩን እንዲመለከት ከጠበቃው ጋር ይነጋገሩ፡፡ በአሜሪካን ግዛቶች የተወለዱ ልጆች ፓስፖርቶች ያሏቸው መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

**የውክልና ስልጣን ማስረጃን ስለመፈረም ከጠበቃዎ ጋር ይነጋገሩ፡፡** የውክልና ስልጣን ማስረጃው በፋይናንስ፣ በልጆች እና በሌሎች የመያዝ ወይም ከስደት የመመለስ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በሚያስተላልፉት ውሳኔዎችን እንዲጠብቅልዎ የሚያምኑትን ግለሰብ እንዲያስቀምጡ ይፈቅዳል፡፡

ለኪራይ ቤት፣ ለምግብ፣ ለመድሃኒቶች እና ለሌሎች ፍላጎትዎ በታገዱበት ጊዜ የሚያሟሉበትን **ገንዘብ ይቆጥቡ፡፡** እርስዎ ታግደው ካሉ ክፍያዎትን እንዲቀበሉ ለቤተሰብ አባልዎ የሚፈቅደውን ሰነድ ስለመፈረም ከአሰሪዎ ወይም ከጠበቃዎ ጋር ይነጋገሩ፡፡

**እስርዎ ከታገዱ/ከተያዙ ዘመድዎ፣ ጓደኛዎ ወይም የማህበረሰቡ አባል ስለእርስዎ ቦርድ እንዲከፍሉ ይጠይቁ፡፡** ይህም ግለሰብ የአሜሪካ ዜጋ ወይም ህጋዊ ቋሚ ነዋሪ (ግሪን ካርድ ያለው መሆን አለበት)፡፡ ከስደት እገዳ/እስር ቤት የሚለቀቀው ቦርድ ብዙን ጊዜ 1500 የአሜሪካ ዶላር ነው ከዛ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የስደት ጉዳይዎ ካበቃ የቦንድ ገንዘቡ ተመላሽ ይሆናል፡፡

**ይሄንን መመሪያ ወይም የአደጋ ጊዜ እቅድ ከመላው ቤተሰብዎ ጋር ይመልከቱ፡፡** በቤተሰብዎ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው ስለመብቶቹ ማወቁን ያረጋግጡ፡፡ ከኃላፊ ጋር በምትገናኝበት ጊዜ ምን ማለት እና ማድረግ እንዳለብዎ በትክክል መለማመድ ይኖርብዎት ይሆናል፡፡

## ማወቅ ያለብዎ መረጃ

የጠበቃዎ የስልክ ቁጥር (ሁልጊዜ የጠበቃዎን የስልክ ቁጥር ግልባጭ ይዘው ይንቀሳቀሱ)፡፡

የቆንስላዎ የስልክ ቁጥር (ሁልጊዜ የቆንስላዎን የስልክ ቁጥር ግልባጭ ይዘው ይንቀሳቀሱ)፡፡

የቤተሰብ አባሉን የስልክ ቁጥሮች

የውጪ ሃገር ተወላጅ /ዜጋ ምዝገባ ቁጥርዎን/ኤ ቁጥር (በስደት ሰነዶቹ ላይ ያለው ቁጥር) የሚፈለግ ከሆነ

ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የገቡበትን ቀን

ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ሲገቡ የነበረው የስደት ሁኔታ

የአሁኑ የስደት ሁኔታው

የወንጀል ታሪክዎ ማለትም እስራቶችን ክሶችን ውጤቶቹን (ከወንጀል ነጻ መሆንዎን) እና ሌሎች ቀኖችን፡፡

## የአደጋ ጊዜ መገናኛ ወረቀት

*ሁሉም የቤተሰብ አባልዎ ይሄንን መረጃ ያለው መሆኑን ያረጋግጡ፡፡*

ጠበቃ/እውቅና የተሰጠው ተወካይ

ስም፡ ____________________

ስልክ ቁጥር፡ ____________________

ቆንስላ

ስም፡ ____________________

ስልክ ቁጥር፡ ____________________

የሃይማኖት ወይም የማህበረሰብ ድርጅቶች

ስም፡ ____________________

ስልክ ቁጥር፡ ____________________

ሌሎች፡ ____________________

ስም፡ ____________________

ስልክ ቁጥር፡ ____________________

ሌሎች፡ ____________________

ስም፡ ____________________

ስልክ ቁጥር፡ ____________________

ሌሎች፡ ____________________

ስም፡ ____________________

ስልክ ቁጥር፡ ____________________



ይህ መረጃ የቀረበው **በካቶሊክ ህጋዊ ኢሚግሬሽን ኔትወርክ አይኤንሲ** ነው፡፡ ለተጨማሪ መረጃ cliniclegal.org. ን ይጎብኙ፡፡

## የመያዣ/ማገጃ ማዕከላት እና ፖሊሲ ጣቢያዎች

*ሁሉም የቤተሰብ አባልዎ ይሄንን መረጃ ያለው መሆኑን ያረጋግጡ።*

የስደት ጉዳት ፍርድ ቤት መረጃ ስርዓት (የመስማት እና የፍርድ ቤት ቀኖች)፡ 1-800-898-7180

አይሲኢ የታሰረ/የታገደ ግለሰብ ቦታ ማሳያ ስርዓት፡ locator.ice.gov

**የሃገር ውስጥ ስደት ማሰሪያ/ማገጃ ማዕከል፡** ______________________________

ስም፡ ______________________________

ስልክ ቁጥር፡ ______________________________

**የሃገር ውስጥ ስደት ማሰሪያ/ማገጃ ማዕከል፡** ______________________________

ስም፡ ______________________________

ስልክ ቁጥር፡ ______________________________

**የሃገር ውስጥ ፖሊስ ጣቢያ፡** ______________________________

ስም፡ ______________________________

ስልክ ቁጥር፡ ______________________________

**የሃገር ውስጥ ፖሊስ ጣቢያ፡** ______________________________

ስም፡ ______________________________

ስልክ ቁጥር፡ ______________________________

---

### የሚወዱት ሰው/ፍቅረኛዎ ከማገጃው ቦታ ወይም ከፖሊስ ጣቢያ ከደወለልዎ መጠየቅ ያለብዎት ጥያቄች፡-

*በተቻለ መጠን ጥያቄዎችን በጥንቃቄ እና በዝርዝር መመዝገብዎን ያረጋግጡ።*

- የህክምና ክትትል ያስፈልግዎታል ወይ?
- እርስዎን የያዘው ወይም ያሰረው የትኛው የህግ አስፈጻሚ ኤጀንሲ ነው?
- ያለኸው የት ነው?
- በአጠገብዎ ያለው ዋና ከተማ ወይም ሌላ ከተማ ምድነው?
- የሰጡህ ወረቀቶች ምድነን ናቸው? የሚሉትስ ምድነው?
- የፍርድ ቤት ቀጠሮ ቀን ወይ የመሰማት ፕሮግራም አለዎ ወይ?
- ከጠበቃዎ/እውቅና ካለው ተወካይዎ ጋር ተነጋግረዋል ወይ?

## የስራ ቦታ ቼክ ሊስት/የማረጋገጫ ዝርዝር

በዚህ መመሪያ ውስጥ ያለውን መረጃ ከስራ ባልደረባዎቹ ጋር ይመልከቱ፡፡ እያንዳንዳቸውም መብቶቻቸውን ማወቃቸውን ያረጋግጡ፡፡ የስደት ጉዳይ ሃላፊዎች በስራ ቦታው ገብቶ በድንገት መያዝ እንደሚችሉ እና ይሄውም፣ 1ኛ በፍቃድ ወረቀት ወይም በ2ኛ ከአሰሪዎ በተሰጣቸው ትእዛዝ ብቻ የሚፈጸም መሆኑን፣

የሰራተኛ ማህበር አባል ከሆኑ እርስዎን እና በችግር ውስጥ ያሉትን ሌሎች የስራ ባልደረቦችዎን ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለብዎ የማህበር ተወካይዎን ይጠይቁ፡፡

የሚቻል ከሆነ ከአሰሪው ጋር ስምምነት ለማድረግ ከማህበር ተወካይ ጋር ይነጋገሩ፡፡ ስምምነቱም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡፡

1. አሰሪው ከህጋዊ ወረቀት ውጪ የስደት ጉዳይ ኃላፊዎች ወደስራ ቦታ እንዲገቡ አይፈቅድላቸውም፡፡
2. አሰሪው የስደት ጉዳይ ሀላፊዎች አሰሪውን ከተገናኙ ለማህበሩ ያሳውቃል፡፡
3. አሰሪው ማህበሩ ሰራተኞችን በጥያቄዎች ላይ እንዲረዳቸው እና ከአደጋ ጊዜ ጋር በተያያዘ እንዲዘጋጁ እንዲረዷቸው የስደት ጠበቃዎቻቸውን እና አቃቤ ህጎቻቸውን ወደስራ ቦታ እንዲያመጧቸው ይፈቅድላቸዋል፡፡
4. አሰሪው በህግ ካልተፈለገ በስተቀር ስም/አድራሻ ወይም የትኛውም የስደት ጉዳይ መረጃን ለፖሊስ ወይም ለስደት ጉዳይ ሀላፊዎች አያቀርብም፡፡
5. አሰሪው የሰራተኛውን የስደት ጉዳይ መረጃ ለመመከት የኮምፒውተር ማረጋገጫ ፕሮግራሞችን አይጠቀምም፡፡

ድንገት በሚያዙበት ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብዎት እቅድ ያውጡ፡፡ ለምሳሌ እያንዳንዱ ግለሰብ ዝም ለማለት እና ላለመሮጥ ቢስማማ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

አሰሪው በድንገት እስርዎ በሚያዙበት ወቅት ከኃላፊዎቹ ጋር ለመነጋገር ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ እርሶ በድንገት በያዙበት ወቅት አሰሪው በቦታው ከሌለ ወይም አሰሪዎ ኃላፊዎቹ እንዲገቡ ከፈቀደላቸው ኃላፊዎቹ መታወቂያ እና ማንኛውም የታደሰ የፈቃድ ወረቀት እንዲያሳዩ እንዲጠየቃቸው ተወካይ ለመምረጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

ግለሰቡ የፈቃድ ወረቀቱን እንዴት ማንበብ እንዳለበት ማወቁን እና የሚያስፈልገው የፈቃድ ወረቀት ምን እንደሆነ ያረጋግጡ፡፡ ለመዘጋጀት እንዲረዳዎ በዚህ መመሪያ ውስጥ ተቀመጡትን የፈቃድ ወረቀቶች መረጃ ይጠቀሙ፡፡


ይህ መረጃ የቀረበው በካቶሊክ ህጋዊ ኢሚግሬሽን ኔትወርክ አይኤንሲ ነው፡፡ ለተጨማሪ መረጃ cliniclegal.org. ን ይጎብኙ፡፡
ኦሪጂናል ጽሁፍ  የቀረበው በካቶሊክ የስደተኝነት ህግ ኔትወርክ፣ ኢንክ (ክሊኒክ)፤ ትርጉም የተሰናዳው በአዩዳ ነው፡፡